የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፩ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 37
ADDIS ABABA 29th May, 2014


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፬/፪ሺ፮ ዓ.ም

ለሦስተኛው የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ....ገጽ ፯ሺ፫፻፺፰


CONTENTS


**Proclamation No. 834/2014**

International Fund for Agricultural Development Financing Agreement for Financing the Pastoral Community Development Project III Ratification Proclamation…. ………………………………………………Page 7398


**አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፬/፪ሺ፮**

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዓቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

ለሦስተኛው የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፶፭ሚሊዮን ፫፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሃምሳ አምስት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዓቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ ዲሴምበር ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፫ በሮም የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

**PROCLAMATION No. 834/ 2014**

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL FUND FOR AGRICULTURAL DEVELOPMENT</u>**

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development stipulating that the International Development Fund for Agricultural Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of SDR 55,300,000 (fifty five million three hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the Pastoral Community Development Project III was signed in Rome on the 16th day of December ,2013;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Additional Financing Agreement at its session held on the 3rd day of April,2014;


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለሦስተኛው የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም ዓቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፬/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **<u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዓቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ ዲሴምበር ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፫ በሮም የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 2000000426 በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. **<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፶፭ሚሊዮን ፫፻ሺ. ኤስ.ዲ.አር (ሃምሳ አምስት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺ. ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፩ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Fund for Agricultural Development Financing Agreement for Financing the Pastoral Community Development Project III Ratification Proclamation No. 834/2014".

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Financing Agreement Number 2000000426-ET signed in Rome on the 16th day of December, 2013 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development is hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of SDR 55,300,000 (fifty five million three hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 29th day of May, 2014.**

***MULATU TESHOME (DR.)***
***PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA***